# *በአገራችን ተመዝግበው ለመስራት ህጋዊ ፈቃድ የሚጠይቁ በውጭ አገር የተመሠረቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን በሚመለከት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስለሚሰጠው አገልግሎት የወጣ ማንዋል*

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማኅበራትን ለመመዝገብና ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 68 (4) መሠረት በውጭ አገር የተመሠረቱ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን በተመለከተ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል የሚከተለው የአሠራር ማንዋል ተዘርግቷል፡፡

## *አንቀጽ 1*
## *ስለ ቃላት ትርጓሜ*

1. "ሚኒስቴር" ማለት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፡፡
2. "ሚሲዮን" ማለት በውጭ አገር የሚገኙ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲዎች፣ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤቶች፣ የቆንስላ ጄኔራል፣ ቆንስላ፣ እና የንግድ ጽ/ቤቶችን ያካትታል፡፡
3. "አዋጅ" ማለት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማኅበራትን ለመመዝገብና ለማስተዳደር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 621/2001 ማለት ነው፡፡
4. "ዳይሬክቶሬት ጄኔራል" ማለት የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ነው፡፡

## *አንቀጽ 2*
## *በአመልካቾች ተሟልተው መቅረብ ስለሚገባቸው ሰነዶች*

በውጭ አገር የተመሰረቱ እና ኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግበው መንቀሳቀስ የሚፈልጉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚያቀርቡት የምዝገባ ጥያቄ እንደሚከተለው ይፈጸማል፡-

1. በውጭ የተመሰረተ የበጎ አድራጎት ድርጅት በአገሩ ወደሚገኘው ወይም ተቀማጭነቱ በሌላ አገር ሆኖ ለአገሩ ወደተወከለው የኢትዮጵያ ሚሲዮን የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርበታል፣

   1.1 የበጎ አድራጎት ድርጅት መቋቋሙን የሚያሳይ ከተቋቋመበት አገር የተሰጠውን የተረጋገጠ ሰነድ (የምስክር ወረቀት)

   1.2 የበጎ አድራጎት ድርጅቱ እንቅስቃሴ እያደረገ የሚገኝባቸውን ዘርፎች የሚያረጋግጥ ፕሮግራምና የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንብ፣

   1.3 የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ኢትዮጵያ ገብቶ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ የድርጅቱ አመራር ቦርድ በፊርማ የተስማማበትና የወሰነበት የተረጋገጠ ደብዳቤ፣

1.4 ድርጅቱ እያካሄደ ካለውና ሊያካሂድ ካቀዳቸው ተግባራት አንፃር የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት ከሚገኝበት አገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ጉዳይ ከሚከታተል አካል የተሰጠው የድጋፍ ደብዳቤ፣

1.5 ድርጅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ለመሥራት ያቀደውን ተግባር የሚያስረዳ ፕሮጀክት ፕሮፋይል እና የወጪ ክፍልፋይ በግልጽ የሚያሳይ ማስረጃ፣

1.6 ድርጅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመስራት የሚመድበው በጀት መጠን፣ እንዲሁም ከጠቅላላ በጀቱ ከ70% የማያንስ ለአላማው ማስፈፀሚያ እና ከ30% ያልበለጠ ለአስተዳደራዊ ወጪ ለማዋል የሚያስችል ዝግጅት ማድረጉን የሚያሳይ ሰነድ፣

1.7 በኢትዮጵያ ድርጅቱን ወክሎ ለሚሰራ አካል የተሰጠ እና የተረጋገጠ ህጋዊ ደብዳቤ፣

1.8 የድርጅቱ ተወካይ የተረጋገጠ ህጋዊ የትምህርት ማስረጃ እና ዝርዝር የማንነት ማስረጃ (CV) ማቅረብ ይኖርበታል፣ የትምህርት ደረጃው ቢያንስ ዲፕሎማ መሆን ይኖርበታል::

1.9 በተጨማሪም ተወካዩ፣

- በአዋጁ አንቀጽ 70 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 በተደነገገው መሠረት የተዘረዘሩት ጉድለቶች የሌሉበት መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣
- ድርጅቱ የተመዘገበበትን ዓላማ ብቻ አክብሮ እንዲንቀሳቀስ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት መሆኑንና ከዚህ ውጭ ሲንቀሳቀስ ቢገኝ በአዋጁ አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች መሠረት በድርጅቱም ሆነ በተወካዩ ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንደሚወሰድበት አስቀድሞ እንዲያውቀው ማድረግ ይገባል::

## *አንቀጽ 3*

## *በውጭ አገር የተመሠረቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ስለሚሰማሩባቸው መስኮች*

1. በአዋጁ አንቀጽ 14 መሠረት በውጭ አገር የተመሠረተ ዓለምአቀፍ የበጐ አድራጐት ድርጅት ዓላማዎች የሚከተሉትን ሊጨምር ይችላል:-

ሀ. ድህነትን ወይም አደጋን መከላከል፣ መቀነስ ወይም ማስወገድ፣

ለ. የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዕድገት እና የአካባቢ ጥበቃን ወይም ማሻሻልን ማፋጠን፣

ሐ. የእንስሳት ደህንነት ማስፋፋት፣

መ. ትምህርት ማስፋፋት፣

ሠ. ጤንነትን ወይም ሕይወት ማዳንን ማራመድ፣

ረ. ጥበብና ባሕልን፣ ቅርስን ወይም ሳይንስን ማዳበር፣

ሰ. አማተር ስፖርትንና የወጣቶችን ደህንነት ማስፋፋት፣

ሸ. በዕድሜ፣ በአካልና በአዕምሮ ጉዳት፣ በገንዘብ ወይም በሌሎች ምክንያቶች የተቸገሩትን መታደግ፣

ቀ. የአገሪቱን የረጅም ጊዜ የልማት አቅጣጫ መሰረት በማድረግ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማበረታታት::

2. በአዋጁ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በሚከተሉት የበጎ አድራጎት ዓላማዎች ላይ ለመሰማራት የሚችሉት የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ብቻ ናቸው::

   በ. የሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ተግባራዊነት ማበረታታት፣

   ተ. የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የጾታ እና የኃይማኖት እኩልነት መረጋገጥን ማበረታታት፣

   ቸ. የህፃናት እና የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበርን ማበረታታት፣

   ኀ. የግጭት አፈታት (ዕርቅን ማስፋፋት) እና

   ነ. የፍትህና የህግ ማስፈፀም አገልግሎቶችን ቀልጣፋነት ማጠናከር፣

   ኘ. ሌሎች ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ የሚደነገጉ ዓላማዎች::

3. ከላይ በአንቀጽ 3 በንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘረው ገደብ፣ በአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) በተደነገገው ሁኔታ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ ዓለም አቀፍና የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም::

## <u>*አንቀጽ 4*</u>

## <u>*የሚሲዮኖች ተግባርና ኃለፊነት*</u>

1. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሚሲዮኖች የሚከናወኑ ተግባራት፣

   1.1 በተወከሉበት አገር የተመሰረተ የበጐ አድራጐት ድርጅት በኢትዮጵያ ተመዝግቦ ለመስራት ጥያቄ ሲያቀርብ በአንቀጽ 2 የተዘረዘሩት ሰነዶች በተሟላ ሁኔታ መቅረባቸውን ያረጋግጣሉ፣

   1.2 ሰነዶቹ ትክክለኛና ህጋዊ መሆናቸውን በሕጉ መሠረት ማረጋገጥ፣

   1.3 ሁለት ኮፒ ለሚሲዮኑ በማስቀረት ዋናውን ለባለጉዳዩ ይመልሳል፣ የተረከባቸውን ሁለት ኮፒ ሰነዶች ለዋናው መ/ቤት ያስተላልፋል፣ መልስ እስኪሰጠው ድረስ ድርጅቱ ቢያንስ ለሃያ ቀናት መጠበቅ እንዳለበት ያሳውቃል::

   1.4 ሚሲዮኑ ከድርጅቱ ከተረከባቸው ሰነዶች በተጨማሪ:-

      1.4.1 ድርጅቱ ወደ ሃገር ውስጥ ገብቶ ቢሰማራ ሃገራችን ከተያያዘችው የልማትና የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመና ደጋፊ ስለመሆኑ፣

      1.4.2 የተቋቋመበት አላማና ፍላጐቱ ለብሔራዊ ሰላምና ደህንነት አስጊ መሆኑን/አለመሆኑን በጥንቃቄ ማጣራት እና የመሳሰሉትን በመጨመር ድርጅቱ ወደ ሃገራችን ገብቶ ቢመዘገብ ከሚያስገኘው ጥቅም አንፃር

በኤምባሲው የሚደገፍ መሆኑን/አለመሆኑን በግልጽ ከሚያስቀምጥ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ ዶክመንቱን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ ከ10 (አስር) ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዳይሬክቶሬት ጄኔራሉ ይልካል::

1.4.3 ድርጅቱ ዓላማውን፣ ግቡንና ተግባሩን በግልጽ ነጣጥሎ ማስቀመጡንና በማረጋገጥ፣ እነዚሁኑ በግልጽ ካላስቀመጠ በአግባቡ እንዲያሟላ በማድረግ መረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ ብቻ ለዳይሬክቶሬት ጄኔራሉ መላክ ይጠበቅበታል::

## *<u>አንቀጽ 5</u>*

## *<u>የዳይሬክቶሬት ጄኔራሉ ተግባርና ኃለፊነት</u>*

1. ዳይሬክቶሬት ጄኔራሉ ከላይ በተዘረዘረው መሠረት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሚሲዮኖች አጣርተው የሚልኩትን አስተያየት እና ሰነዶች በመመርመር ለመመዝገብ ጥያቄ ያቀረበው ድርጅት ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ቢሰራ የሚኖረውን እንድምታ በመገምገም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አቋም ምን መሆን እንዳለበት የሚገልጽ ማስታወሻ ዶክመንቶቹን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ በሁለት ቀን ውስጥ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ያቀርባል::
2. ዳይሬክቶሬት ጄኔራሉ የበላይ ኃላፊዎች ውሳኔ በደረሰው ዕለት ወይም በሚቀጥለው ቀን ከሚመለከተው ሚሲዮን የመጣለትን ሰነድ ለበጐ አድራጐት ድርጅቶች እና ማኀበራት ምዝገባ ኤጀንሲ ይልካል::
3. ኤጀንሲው የሰጠው ውሳኔ ለዳይሬክቶሬት ጄኔራሉ እንደደረሰው ዳይሬክቶሬት ጀነራሉ ይህንኑ በዕለቱ ወይም በሚቀጥለው ቀን ለሚሲዮኑ ያሳውቃል::
4. የሚመለከተው ሚሲዮን ከዳይሬክቶሬት ጄኔራሉ የተላከለትን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ውሳኔውን ለድርጅቱ ቢዘገይ በሁለት ቀን ውስጥ ያሳውቃል:: ይህንኑ ማድረጉን ለዳይሬክቶሬት ጄኔራሉ እና ለኤጀንሲው በግልባጭ ያሳውቃል::
5. ድርጅቱ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ እንዲሰራ የተፈቀደለት ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ማስረጃዎቹን አሰባስቦ ስለትክክለኛነታቸው ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማረጋገጫ ከተሰጠው በኋላ ወደ በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማኀበራት ኤጀንሲ ሄዶ የምዝገባ ሂደቱን ይጀምራል::

## *<u>አንቀጽ 6</u>*

## *<u>ማንዋሉ በተግባር ላይ ስለሚውልበት ጊዜ</u>*

1. ይህ ማንዋል በሚኒስትሩ ተፈርሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ጥር 27 ቀን 2002 ዓ.ም